# የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቻቸው በጋብቻ ውስጥ!
# Causes of Conflict and Suggested Solutions in Marriage!

ፓስተር ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ
(ላይሰንስድ ክሊኒካል ፓስቶራል ካውንስለር)
ካሊፎርንያ ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ
ግንቦት 5, 2007 ዓ.ም

Pastor Dr. Mulatu Belayneh, Licensed Clinical Pastoral Counselor- Advanced Certified (LCPC)
California, United States of America
May 13, 2015

ቅጽ.1፡ - " በመጀመሪያዎቹ አስርተ ዓመታት የጋብቻ ዘመናት ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ ግጭቶች፣ የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው!"


ፓስተር ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ
(ላይሰንስድ ክሊኒካል ፓስቶራል ካውንስለር)
ካሊፎርንያ ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ


ግንቦት 5, 2007 ዓ.ም

The Most Common Areas of Conflicts in the First Ten Years of Marriage and Suggested Solutions!"


Pastor Dr. Mulatu Belayneh, Licensed Clinical Pastoral Counselor- Advanced Certified (LCPC)
California, United States of America


May 13, 2015


Printed in California, United States of America
Bang printing
28210 N. Avenu Stanford
Valencia, CA 91355



Copyright
All rights reserved. No part of this book may be reproduced in any form or by any electronic or mechanical means, including information storage and retrieval systems, without permission in writing from the publisher, except by a reviewer who may quote brief passages in a review.
አሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማባዛት፣ በኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች መቅረጽና ማራባት የተከለከለ ነው፡፡



Editing:-Desyibelew Demmissie
Texting Formating: Yared Gezai
Cover Design: Asfaw Berhe


## መታሰቢያነቱ

1. የእግዚአብሔር ድንቅ ስጦታና የትዳር አጋር ለሆነች ለባለቤቴ ለእመቤት ታደሰ( እሙ) በእኔ አጠራር " እናት" የትዳርንን ምንነት፣ በረከትነት፣ በሕይወትና በአገልግሎት በሚገጥሙ በከፍታም ሆነ በዝቅታ፣ በጤንነትም ሆነ በሕመም፣ በማግኘትና በማጣት፣ በስኬትና ባልተሳካ ወቅት፣ በሕይወት በሚገጥሙና በሚፈራረቁ የተለያዩ ገጽታዎች ሁሉ ታማኝ ሚስት፣ እናት፣ እህት፣ ጓደኛና በእውነተኛ ልብና አመለካከት መካሪና ገሳጻጭ ለሆነችና እንዲሁም እውነተኛ የትዳርን ምንነት፣ አስፈላጊነትና ተግዳሮት በጋራ እንድለማመድ ዕድል ለሰጠችኝ ለሚስቴ ይሁን!!
2. የአምላክ ዕጹብ ድንቅ ፍጡርና ስጦታ ለሆኑ ለሁለት ወንድ ልጆችችን ለናታንና ለኖህ ሙላቱ ( To Nathan & Noah Mulatu) የአባትነት ወግ፣ ሚናና ኃላፊነት እንድለማመድ፤ ደግሞም የእግዚአብሔርን አባትነት ለእኛም ሆነ ለልጆቻችን እንዴት እንደሆነ ይበልጥ እንድረዳና በአባትነቱ እንድደነቅ ዕድል ለሰጡኝ ለልጆቻችን ይሁልንኝ!

## ስጦታ

ከ፡ ____________________

ለ፡ ____________________

ቀን፡ ____________________

ፊርማ፡ ____________________

## የአንባቢያን አስተያየት

ጋብቻ ባልና ሚስት ጨርሰው የማይመረቁበት ትምህርት ቤት ነው:: በተለይ ተጋቢዎች በመጀመሪያዎቹ የጋብቻ ዕድሜያቸው ብዙ የማያውቁትና ያልተለማመዱት ነገር ስለሚኖር፣ በቀላሉ ሊፈቱ የሚችሉ ግጭቶች ግንኙነታቸውን አደጋ ላይ ሊጥሉ ይችላሉ። ይህ መጽሐፍ በዚህ ወቅት የሚከሰቱ ግጭቶችንና መንስኤዎቻቸውን በመተንተን የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ይጠቁማል። ስለዚህ ባለማወቅ ምክንያት የሚከሰተውን የጋብቻ ችግሮችንና አሉታዊ ውጤቶቹን ለመቅረፍና ለማስወገድ የሚያግዛችሁን ይህን መጽሐፍ እንድታነቡ እመክራለሁ::

**ከበደ በከሬ**
**የሥነልቦና አማካሪና ፀሐፊ**

የዚህች መጽሐፍ ዋና ዓላማ በትዳር ውስጥ የሚያጋጥሙ ግጭቶች ምንነትን፣ መንስኤዎቻቸውንና መፍትሔዎቻቸውን በዝርዝር በማብለጥ ክርስቲያን ትዳራቸውን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ምሪት በማስተዳደር የተባረከ ሕይወት ለመኖር እንዲችሉ ነው። ዶ/ር ሙላቱ ይህንን ትምህርት ዋና ዋና መመሪያ የሆኑትን ነጥቦች በአራት ዓበይት ክፍሎች የግጭት ዓይነቶች፣ መንስኤዎቻቸውንና ከነመፍትሔቻቸው አንባቢው ሊረዳውና ሊጠቀምበት በሚችልበት መንገድ በዝርዝር አቅርቧል። ግጭት በመላው ጋብቻ ዘመን ሁሉ የሚከሰት ስለሆነ በጋብቻ ዘመናት ሁሉ ለሚገኙትም የሚጠቅም ነው። አብያተ ክርስቲያናት የአባላቶቻቸውን የትዳር ሕይወት ለማሳደግና ጽኑ ቤተሰብን ለማፍራት ሲያስተምሩ ይህችን መጽሐፍ እንደ ማስተማሪያ መጽሐፍ ቢጠቀሙባት በጣም ትረዳለች።

**ሥዩም ገብረየሱስ**
**የቤተሰብ ኅብረት አገልግሎት ክፍል የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስትያን ቤተ ክርስቲያን ዳላስ ቴክሳስ**

ይህን መጽሐፍ ትዳራችንን እንደ እግዚአብሔር ሰው በመንፈሳዊ እንደ ባለ አእምሮ በጥበብ ለመምራት ጠቃሚ ነው።

**ዶ/ር ብሩክ ታፈሰ አማረ (M.D)**
**የማህጸን ስፔሻሊስትና አሁን ደግሞ በሰሜን አሜሪካ የውስጥ ደዌ ሐኪም**

ክርስቲያናዊ ትዳር ለመምሥረት ለምታስቡ ሰዎች፣ ከጋብቻ በኋላ በተለያዩ ትዳር ነክ ችግሮች ውስጥ በማለፍ ላላችሁ ባለትዳሮች፣ እንዲሁም በትዳርና በቤተሰብ ዙሪያ የማስተማርና የማማከር ሸክም ለተቀበላችሁ አገልጋዮች ሰፋ ያለና ጠቃሚ እውቀት የያዘች መጽሐፍ በመሆንዋን ስለተገነዘብሁ በእጃችሁ ውስጥ እንድትገባ አሳስባለሁ።

**ኢንጅነር ተካ ገብሩ የጋብቻና ቤተሰብ አማካሪ**

የትዳር ሕይወት ምን መሆን እንደሚገባና ሚዛኑን በጠበቀ ደረጃ የተሰናዳ የሚያስተምር መጽሐፍ እንደሆነ አንብቤዋለሁ እንዲሁም ሁሉም በጋብቻ ውስጥ ያሉ ሁሉ ቢያነቡት ተጠቃሚ ይሆናሉ እላለሁ።

**ፓስተር አሸብር በላይነህ**

**መ/ቅ/ዓ/አ/ቤ.ክ የትምህርት ክፍል ዋና ኃላፊና በአመራር የድህረ ምረቃ ዲግሪ ተማሪ**

ዶ/ር ሙላቱ በትዳር ውስጥ የሚነሱትን ግጭቶች በፍች ከማሳረግ ይልቅ እንደመረማመጃ ድንጋዮች በመጠቀም ወደፊት ለመስፈንጠር የሚረዱ እጅግ ጠቃሚ ትምህርቶችንና ምክሮችን አብርክቶልናል። አንኳር የሚባሉ ጉዳዮችን አንስቶ የግጭቶችን ውል እያስጨበጠና ውስብስቡን መፍቻ መንገድ እየጠቆመ ሩጫ አቋርጦ ከመሸነፍ ማሸነፍ የሚቻልበትን ቀና ጎዳና እንድንይዝ በጥበብና በእውቀት አቅጣጫዎችን አመላክቶናል። በማንበቤ ልብ ብያለሁ አንብቡና ልብ በሉ!

**ወንድም ዮናስ አረፋይኔ የኢትዮጵያ ጉባኤ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ዋና ጸሐፊ**

በተለያየ የዕድሜ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ክርስቲያኖች ከትዳር ሕይወት ጋር በተያያዘ ሁለንተናዊ የሆነ እይታ የሚሰጥና ችግሮችንም ሆነ መፍትሔዎቻቸውን በጥልቀት የሚያሳይ ጥናትን መሠረት አድርጐ በአማርኛ የተጻፈ መጽሐፍ ማግኘት አስቸጋሪ ሆኖ ይታያል፡፡ ከዚህ አኳያ ይህ የዶ/ር ሙላቱ በላይነህ መጽሐፍ ያለውን ክፍተት ለመሙላት አንድ እርምጃ ነው፡፡ መጽሐፉ በተለይ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆችና ት/ቤቶች፣ ሰባኪዎች፣ አስተማሪዎችና የጋብቻ አማካሪዎች ለማስተማሪያ ቢጠቀሙበት የሚረዳቸው በርካታ መረጃዎችንና ትምህርቶችን የያዘ ጠቃሚ መጽሐፍ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

**ዶ/ር ንጉሤ ተፈራ(PhD)**

ይህ መጽሐፍ የአሳብ ፍሰቱ፣ የአጻጻፉና የአቀራረቡ ብስለትና ጥራት ያለው ከመሆኑም በላይ የእግዚአብሔርን ቃል ማዕከል ያደረገ ስለሆነ በጋብቻ ውስጥ ግጭትን እየፈቱ ደስተኛና ጤነኛ የትዳራ ግንኙነት እንዲኖራቸው ለሚሹ ጥንዶች ሁሉ መሠረታዊ እውቀትን የሚያስጨብጥና ወቅታዊ መጽሐፍ ነው። የመጽሐፉ ዝግጅት ጥንዶች በግል በጥሞና ጊዜያቸው፣ በቤተ ክርስቲያን ያሉ ባለትዳሮች በቡድን በመሆን ሊያጠኑትና ሊወያዩበት የሚችሉበትና የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች፣ አስተማሪዎች፣ የጋብቻና የቤተሰብ አማካሪዎች እንዲጠቀሙበት ሆኖ የተዘጋጀ ብዙ ቁም ነገሮችን ያዘለ መጽሐፍ መሆኑን ተመልክቻለሁ።

**እህት ደብረወርቅ መኮንን የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን የቤተሰብና የማማከር አገልግሎት ክፍል ሎስ አንጀለስ**

ፓስተር ሙላቱ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ፣ በብዙ ትክክለኛ ሳይንሳዊ መርጃዎችም የተደገፈ ፣ለትዳር ስለልጆች አስተዳደግና ልጅ ከመውለድ በኃላ በእናቶች ጤና ላይ ሊከሰቱ የሚችሉትን የጤና እክሎች፥ መንስሔዎችና መፍትሔዎቻቸውን በቀላሉ ለመረዳትና አሳቡን ለመከተል በሚያስችል መልኩ ይህን መጽሐፍ አቅርቦልና። ይህን መጽሐፍ ወደ ትዳር ሊገቡ በዝግጅት ላይ ያሉና በማንኛውም የጋብቻ ዘመን ያለን ሁላችን ይህንን መጽሐፍ አንብበን ተጠቃሚዎች እንድንሆን አበረታታለሁ።

**ዶ/ር ደረጀ ሳህለ እዮ( M.D)**

**Pulimonary Disease, Critical Care and sleep Disorder Fort Worth lung Clinic**

ይህ መጽሐፍ አብዛኛውን ቤተሰብ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ሰፋ ባለ ሁኔታ የሚዳስስ ፣ የጋብቻና የቤተሰብ ጉዳዮች ላይ ጠቃሚ እውነቶችንና ተግባራዊ የሆነ ግንዛቤዎችን የሚያስጨብጥ ሁኖ አግቸዋለሁ። በዚህ መጽሐፍ የተነሱት ዋና ዋን ርዕሶች መካከል ጥቂቱን በመጥቀስ ይበልጥ አስፈላጊነቱን ለማጉላት እፈልጋለሁ። የባለትዳሮች የአልጋ ጉዳይ ግልጥነትና ጨዋነት በተላበስ ሁኔታ መቅረቡ፣ በጋብቻና በቤተሰብ ሕይወት ተግዳሮት የሆነዉን የዘመኑ ፈተና ስለፖርኖግራፊ በሰፊው መዳሰሱ፣ በሁሉም የግንኙነት መስመሮች ተግዳሮት የሚሆኑበትን የግጭት ምክንያቶችን ለመፍታት የሰመረ ተግባቦት አስፈላጊነትና በጋብቻና በቤተሰብ ሕይወት ትምህርት ፍችን በተመለከተ ከማውገዝና እግዚአብሔር የሚጠላው መሆኑን አበክሮ ከመናገር ያለፈ ብዙ አይባልም ነገር ግን በዚህ መጽሐፍ ዉስጥ ስለ ፍች የቀረበው መሠረታዊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች፣ የሚያስከትለው መጠነ ሰፊ ቀውስ፣ የተሰጡት የመፍትሔዎች አሳቦችና በተለይ ስለ ይቅርታ በተሰጠው ትምህርት ይቅርታን መለማመድ አማራጭ የሌለውን ክርስቲያናዊ ግዴታችንን መሆኑን በአጽንዎት የሚያሳስብ ሆኖ አግቸዋለሁ። ይህ መጽሐፍ ትዳር ለሚያስቡ፣ ትዳር ለጀመሩ፣ በትዳርም የቆየነውንና በማማከር አገልግሎት ላይ ያለነው ሁላችን ልናነበውና እንደ ማጣቀሻ ልንጠቀምበት የሚገባ መጽሐፍ ነው እላለሁ።

**ወ/ሮ ስንቅነሽ እዘነ**

**የቤተሰብ ሕይወትና የጋብቻ የማማከር አገልግሎት በኢ.ሙ.ወ.ማ.ቤ/ከ መካከለኛው ቀጠና አዲስ አበባ**

## ማውጫ

ገጽ


ክፍል አንድ(1)፦ የጋብቻ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች ............ 1

ምዕራፍ አንድ(1)፦ የጋብቻ ትርጉምና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቱ ........ 2

I. የጋብቻ ምንነት ............ 2
II. ጋብቻ ለሰው ልጆች የተሰጠበት ዓላማ ............ 5
III. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጋብቻ መርህ ............ 6
IV. ጋብቻ የሚጠይቀው የየግል ኃላፊነትና ተጠያቂነት ............ 8
V. የጋብቻ አጠቃላይ ባህርይ /ተፈጥሮ/ ............ 9
VI. የጋብቻ የላቀ ምሳሌነት ............ 10

ክፍል ሁለት(2)፦ የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው 14

ምዕራፍ ሁለት(2)፦ የግጭት ምንነትና አይቀሬነት ............ 15

I. የግጭት ምንነት ............ 15
II. በባለትዳሮች መካከል የግጭት አይቀሬነት ............ 20

ምዕራፍ ሶስት(3)፦ ግጭትን በወቅቱ በጋራ ያለመፍታት የሚፈጥረው ተጽዕኖ ............ 34

I. በጥንዶች የፍቅር ግንኙነት ላይ ............ 34
II. በጥንዶች ሁለንተናዊ ማንነት ላይ ............ 37

ምዕራፍ አራት(4)፦ የተለያዩ የለውጥና የሽግግር ደረጃዎች ............ 42

I. የተለያዩ የለውጥ ደረጃዎች ምንነት ............ 42
II. በጥንዶች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ የተለያዩ ለውጦች ............ 42
III. የተለያዩ ወቅታዊ የለውጥ ደረጃዎችና ባህሪያቸው ............ 46

ምዕራፍ አምስት(5)፦ በጋራ መወሰን /ውሳኔ አሰጣጥ/ ............ 53

I. በጋራ የመወሰን ምንነት ............ 53
II. በጋራ የመወሰን አስፈላጊነት ............ 53
III. በጋራ በመወሰን ሂደት ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች ... 55
IV. በጋራ በመወሰን ሂደት ላይ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ............ 59

ምዕራፍ ስድስት(6)፦ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ............ 64

I. ቤተሰብና የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ምንነት ............ 64
II. አባትንና እናትን መተው ............ 64
III. በቤተ ዘመድ ጣልቃ ገብነት ለግጭት ሊያጋልጡ የሚችሉ መንስኤዎች ............ 67
IV. በቤተ ዘመድ ጣልቃ ገብነት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ............ 71

**ምዕራፍ ሰባት(7)፦ ተግባቦት /ኮሙኒኬሽን/** ........ 76
I. የተግባቦት /የኮሙኒኬሽን/ ምንነት ........ 76
II. ከተግባቦት /ኮሙኒኬሽን/ ጋር ተያይዘው ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች ........ 78
III. በተግባቦት /በኮሙኒኬሽን/ ላይ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መንስኤዎች መፍትሔዎች ........ 85
**ምዕራፍ ስምንት(8)፦ ገንዘብና ንብረት** ........ 93
I. የገንዘብና ንብረት ምንነት ........ 93
II. ከገንዘብና ከንብረት ጋር የተያያዙ የግጭት መንስኤዎች ........ 93
III. በገንዘብና በንብረት ምክንያት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ........ 103
**ምዕራፍ ዘጠኝ(9)፦ የግብረ ስጋ ግንኙነት** ........ 109
I. የግብረ ስጋ ግንኙነት ምንነት በትዳር ውስጥ ........ 109
II. በክርስቲያን ትዳር ሕይወት የግብረ ስጋ ግንኙነት /ሩካቤ ስጋ/ ዓላማ 110
III. ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር የተያያዙ የግጭት መንስኤዎች ........ 113
IV. በግብረ ስጋ ግንኙነት ምክንያት ለሚፈጠሩት ግጭቶች መፍትሔዎች ... 122
**ምዕራፍ አስር(10)፦ የእምነትና የመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት** ........ 131
I. የእምነትና የመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት ምንነት ........ 131
II. በመንፈሳዊ ሕይወትና መረዳት ልዩነት መሠረት የግጭት መንስኤዎች ........ 131
III. በመንፈሳዊ ልዩነት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ........ 136
**ምዕራፍ አስራ አንድ(11)፦ የባልና የሚስት ኃላፊነትና የተለያየ ሚና** ... 143
I. የክርስቲያን ባልና ሚስት ሚና ምንነት ........ 143
II. ከባልና ሚስት ኃላፊነትና ሚና ጋር የተያያዙ የግጭት መንስኤዎች ........ 143
III. ከባልና ሚስት ኃላፊነትና ሚና ጋር በተያየዘ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ........ 148
**ምዕራፍ አስራ ሁለት(12)፦ ፖርኖግራፊ** ........ 156
I. የፖርኖግራፊ ምንነት ........ 156
II. የፖርኖግራፊ መስፋፋት ........ 156
III. የተጠቃሚዎች አመለካከት ........ 157
IV. ፖርኖግራፊ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታ ........ 159
V. ባለትዳሮችን ለፖርኖግራፊ ሱስ ተጋላጭ የሚያደርጉ ምክንያቶች ........ 161



VI. የፖሮኖግራፊ ሱስ አሉታዊ ተጽዕኖ ........ 164
VII. በፖርኖግራፊ ሱስ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ........ 167
**ክፍል ሶስት(3)፦ ቅድመ ወሊድ፣ ወሊድና ድህረ ወሊድ** ........ 177
**ምዕራፍ አስራ ሶስት (13)፦ መውለድ አለመፈለግና አለመቻል** ........ 178
I. መውለድ አለመፈለግና አለመቻል ........ 178
II. ባለመውለድ ምክንያት ሊፈጠሩ ለሚችሉ ግጭቶች መፍትሔዎች ........ 181
**ምዕራፍ አስራ አራት(14)፦ ወሊድን መቆጣጠር** ........ 193
I. ወሊድን የመቆጣጠር ምንነት ........ 193
II. በወንጌላዊያን ክርስቲያኖች መካከል ያሉ የተለያዩ አመለካከቶች ........ 193
III. የተለመዱ የቤተሰብን ቁጥር የመመጠን ምክንያቶች ........ 194
IV. የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ ዓይነቶች ........ 195
V. የወሊድ መቆጣጠሪያ ተጠቃሚ በመሆን ወቅት ........ 198
**ምዕራፍ አስራ አምስት (15)፦ እርግዝናና ከእርግዝና ጋር የተያያዙ ክስተቶች** ........ 202
I. የእርግዝና ምንነት ........ 202
II. በእርግዝና ወቅት የሚፈጠሩ ለውጦች ........ 203
III. በእርግዝና ወቅት ለሚፈጠሩ ችግሮች መፍትሔዎች ........ 205
**ምዕራፍ አስራ ስድስት(16)፦ ያልተፈለገና ያልታሰበ እርግዝና** ........ 212
I. ያልተፈለገና ያልታሰበ እርግዝና ምንነት ........ 212
II. ያልተፈለገና ያልታሰበ እርግዝናና ወሊድ ወቅት ሊወሰዱ የሚገባቸው መፍትሔዎች ........ 213
**ምዕራፍ አስራ ሰባት(17)፦ ከወሊድ በኋላ ሊፈጠር የሚችል ትኩረት የሚያሻው ለውጥ** ........ 218
I. ድህረ ወሊድ ድብርት ........ 218
II. የድህረ ወሊድ ድብርት መንስኤዎች ........ 218
III. ድህረ ወሊድ ድብርት የሚያመጣው ተጽዕኖ ........ 219
IV. ድህረ ወሊድ ድብርትን ተቋቁሞ ደስተኛ ባለትዳር ለመሆን ........ 219
**ምዕራፍ አስራ ስምንት(18)፦ የመጀመሪያና ልጅና ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን ማሳደግ** ........ 227
I. የመጀመሪያ ልጅና ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን የማሳደግ ምንነት ...... 227

I. የመጀመሪያና ልጅንና ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን በማሳደግ ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች ........ 228
II. የመጀመሪያ ልጅንና ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን በማሳደግ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ........ 234

**ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ (19)፡- የእንጀራ ልጅን ማሳደግ** ........ 244

I. የእንጀራ ልጅ ምንነት ........ 244
II. የእንጀራ ልጅን በማሳደግ ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች ........ 245
III. የእንጀራ ልጅን በማሳደግ ሂደት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ........ 249

**ምዕራፍ ሃያ (20)፡- ልጆችን በአግባቡ በመቅጣት ማሳደግ** ........ 254

I. ልጆችን በአግባቡ በመቅጣት የማሳደግ ምንነት ........ 254
II. ልጆች በመቅጣት ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች ........ 255
III. ልጆችን እየቀጡ በማሳደግ ሂደት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ........ 260

**ምዕራፍ ሃያ አንድ (21) በቂ እንቅልፍ ማጣት** ........ 265

I. የበቂ እንቅልፍ ምንነት ........ 265
II. የእንቅልፍ አስፈላጊነት ........ 266
III. በቂ እንቅልፍ ማጣት የሚያስከትለው ተጽዕኖ ........ 267
IV. በቂ የሆነ እንቅልፍ በማግኘት የትዳርና የቤተሰብን ጤንነት ለመጠበቅ የሚረዱ መፍትሔዎች ........ 270

**ክፍል አራት፡- እርቅ፣ የፍች ሂደትና ከፍች በኋላ አዲስ ቀጣይ ኑሮ** ........ 275

**ምዕራፍ ሃያ ሁለት (22)፡- ፍችና የፍች ሂደት** ........ 276

I. የፍች ምንነት ........ 276
II. ፍች በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ ........ 276
III. ስለፍች የተለያዩ አመለካከቶች ........ 277
IV. የፍች ደረጃዎች ........ 278
V. በፍች ሂደት በሚያልፉ ጥንዶች ላይ ሌሎች ሰዎች ሊፈጠሩባቸው የሚችሉ የተለያዩ ስሜቶች ........ 283
VI. ይቅርታና እርቅ ........ 286
VII. በባለትዳሮች መካከል እርቅ ያስፈለገበት ምክንያት ........ 291
VIII. እውነተኛ እርቅ የሚጠይቀው ........ 294
IX. ለእውነተኛ እርቅ መዘጋጀት ........ 296

**ምዕራፍ ሃያ ሶስት (23)፡- ከፍች በኋላ አዲስ ቀጣይ ኑሮ** ........ 300

I. ከፍች በኋላ የአዲስ ቀጣይ ኑሮ ምንነት ........ 300



II. ከፍች በኋላ አዲስ ቀጣይ ኑሮ ለመለማመድ ጥረት የማድረግ አስፈላጊነት ........ 301
III. በፍች ሂደት እያለፉ ያሉትን ወደ ፊት መጓዝ እንዲችሉ የማገዝ አገልግሎት ........ 303

**ማጣቃለያ** ........ 312

**ዋቤ መጽሐፍት** ........ 313

**ስለጸሐፊው** ........ 316

## ምስጋና

1. ከሁሉ አስቀድሜ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከዘላለም ሞት ለአዳነኝ፣ ለአገልግሎቱ ታማኝ አድርጎ ለጠራኝና ለቆጠረኝ ብሎም ይህን መጽሐፍ እንድጽፍ በብዙ መንገድ የረዳኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።
2. የእግዚአብሔር ድንቅና ውብ ስጦታ የሆነችውን ውድ ባለቤቴን ወ/ሮ እመቤት ታደሰን ( እሙ) እንደ እኔ አጠራር "እናት" የትዳር ምንነት፣ በረከት፣ ኃላፊነት ለማጣጣምና መመረቅ በሌለበት የትዳር ሕይወት ትምህርት ቤት በመማር ሂደት ውስጥ እንድሆን በብዙ ነገርና መንገድ ከጎኔ ለማትለየው ባለቤቴን ከልቤ ላመሰግን፣ ለእርሷ ያለኝን ፍቅርና አክብሮት ልገልጽ እወዳለሁ!
3. የትዳርና የቤተሰብን በረከት፣ ደስታ፣ ኃላፊነት እንድለማመድ ብሎም መጽሐፉን ስጽፍ ይበልጥ የግል የትዳርና የቤተሰብ ሕይወቴን እንድቃኝና እንደ ልጆች ከአባታቸው ከሚያገኙት ጊዜ በመስጠት እንድጽፍ ዕድል ለሰጡኝ የአምላክ ስጦታችን ለሆኑት ናታንና ኖህ ሙላቱ በአባትነት ፍቅር ላመሰግን እወዳለሁ።
4. ለተወሰኑ ወራት ከእኛ ጋር በመሆን ልጆችንና እኛን በመንከባከብ ጊዜና ምቹ ሁኔታዎችን በማግኘት እንድጽፍ ለተባበረችኝ ወላጅ እናቴ ለወ/ሮ የሽጥላ ካ (ማማየ) እንዲሁም ለመምጣቷና ከእኛ ጋር ለመቆየቷ በደስታ በመፍቀ ለተባበረን ለአባቴ ዋና ሳጅን በላይነህ በለጠ (ባባ) ሳላመሰግን አላልፍም።
5. የመጽሐፉን ንድፍ በማንበብ የተለያዩ እርማቶችንና ማስተካከያ ሥራ ለአከናወነል ወንድም ደስይበለው ደምሴ፣ የመጽሐፉን ሽፋን ዲዛይን በማድረግ ለተባበረ ወንድም አስፋው በርሔ እንዲሁም ጊዜ በመወሰድ ጽሑፍን የመጽሐፍ መል እንዲይዝ ጽሑፉን በማቀናጀት የተባበረኝን ወንድሜን ያሬድ ገዛኢን ከል አመሰግናለሁ።
6. የመጽሐፉን ንድፍ በማንበብ ጠቃሚና አበረታታች አሳብና ሙያዊ ምክር ለለገሱ የእግዚአብሔር ሰዎች፦ ወንድም ጋሽ ተካ ገብሩ (ኢንጅኔር) ፣ ዶ/ር ንጉሴ ተፈራ ፣ ወንድም ጋሽ ስዩም ገብረየስ፣ ወንድም ከበደ በከሬ ፣ እህት ደብረወርቅ መኮንን ፣ ፓ/ር አሸብር በላይነህ፣ ዶ/ር ብሩክ ታፈሰ፣ ወንድም ዮናስ አረፋይኔ፣ ወ/ዊ ዳዊት ቆጢሶ፣ እህት ስንቄ አዘነ እና ዶ/ር ደረጀ ሳህለ ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ።
7. የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ሎስ አንጀለስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ አገልጋዮች፣ ምዕመናንና በሰሜን አሜሪካ ባለች ኢትዮጵያንና ኤርትራዊያን አብያተ ክርስቲያናት በራቸውን በመክፈት እና በአካል፣ በስልክና በስካይፕ በማማከር አገልግሎቴ ተጠቃሚ ለነበራቹህ ለመጽሐፉ ከብዙ አቅጣጫ እንድመለከትና እይታየ እንዲሰፋ እድል ስለሰጣችሁኝ እናንተንም ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ላቀርብ እወዳለሁ።



8. በተለያየ መንገድ የመጽሐፉ ረቂቅ ተጠናቆ ለአንባቢ እንዲተዋወቅ ባለው ሂደት በብዙ አቅጣጫ የተባበሩኝ ወንድም አልዓዛር ጌታቸው እና ወንድም ነብዩ ኢያሱን እንዲሁም በተለያየ አቅጣጫ ድጋፋቹህ ላልተለየኝ የእግዚአብሔር ሰዎች በሙሉ ከልብ አመሰግናለሁ።
9. በኢትዮጵያና በአፍሪካዊያን ሕብረተሰብ መካከል የተሻለ ሁለንተናዊ የሆነ ጤንነት እንዲኖር ለማበረታታት፣ ለማስተማርና አስፈላጊውን የሕክምና አገልግሎት ከመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ሕብረተሰቡ ማግኘት እንዲቻል ታስቦ ለተቋቋመና እየሠራ ላለ መንግሥታዊ ላልሆነ ድርጀት " ***African communities public Health Collation (ACPHC)"*** ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ስለሰጠን የተለያዩ ትምህርትና ስልጠናዎች ዕድል ለመጽሐፌ ይበልጥ አይታየን ስላሰፋልኝ ከልብ ላመሰግንና ድርጅቱም ይበልጥ ይስፋ፣ ይጠንክርና ሕብረተሰቡን እንደሚገባ ማገልገሉን ይቀጥል በማለት ልባዊ ምኞቴን ልገልጽ እወዳለሁ።
10. በዙሪያችን ላሉ ቤተሰቦች፣ ወንድሞች፣ እህቶችና ወዳጆች የእናንተ የተለያዩ ድጋፋቹህ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በትዳራችን፣ በቤተሰባችን፣ በሕይወታችንና በአገልግሎታችን ያላችሁ አስተዋጾ ቀላል አይደለምና እግዚአብሔር ይባርካችሁ ለማለት እወዳለሁ።

### Special Thanks

I would like to give a very special thanks to the West Angeles Church of God in Christ counseling Center, Administrative and Clinical staffs. I can't forget your generosity for granted me a scholarship to continue my education and license. I am so great full for the opportunity each one of you gave me to learn from your experience. God Bless you all.

## ስለመጽሐፉ አጻጻፍና አቀራረብ ስልት አጭር መግለጫ

**የመጽሐፉ አቀራረብ**

1. መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በአደረገ
2. በተግባራዊ ልምምድ የተጠናከረና
3. በክሊኒካል እና ክርስቲያናዊ ስነ ልቦና ላይ የተደገፈ

**የመጽሐፍ አጻጻፍ ስልት**

1. ምንነትን በማስረዳት
2. ችግሮችን ለይቶ በማስቀመጥና
3. ለችግሮቹ መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉትን በመዘርዘር ግጭትን እየፈቱ ደስተኛ የሆነ ትዳርና ጤነኛ የሆነ ግንኙነት በመፍጠር መልካም ቤተሰብ መመሥረት እንዲቻል ታስቦ የተጻፈ መጽሐፍ ነው።
4. ለጥንዶችና ለቡድን የሚሆን የውይይት ጥያቄዎችን የያዘ

**የመጽሐፉ ተደራሲያን**

1. በዚህ የጋብቻ ዘመን ክልል ያሉ ባለትዳሮች
2. በቅርብ ሊጋቡ በዝግጅት ላይ ላሉ እጮኛሞች
3. ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች
4. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማማከር አገልግሎት እያገለገሉና ሊያገለግሉ ለሚያስቡ
5. በተለያየ የትዳር ዘመን ላይ ላሉ ነገር ግን ራሳቸውን ለመመርመርና ለመማር ብሎም የሚቀጥለው በሌሎች የጋብቻ ዘመናት ላይ ያሉ የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎች ታትመው እስኪወጡ ድረስ ትክክለኛ አንድ ወጥ የሆነ መረጃና ማስረጃ እንዲኖራቸው የሚረዳ መጽሐፍ ነው።



## መቅድም

ፓስተር ዶ/ር ሙላቱ ከዚህ ቀደም የአገልግሎት ተግዳሮቶች እና መፍትሔዎቻቸው በሚል ርዕስ መጽሐፍ ማሳተሙና ለአንባቢ ማቅረቡ ይታወቃል። ይህም መጽሐፍ ለብዙዎች መታነጽ ምክንያት እንደሆነ የአነበብነው ሰዎች ምስክሮች ነን። አሁን ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሁላችንንም የትዳር ሕይወት የሚቃኝ ጠንከር ያለ ትምህርትና ምክር የያዘ ወቅታዊ መጽሐፍ በጋብቻ ዙሪያ አበርክቶልናል። ያገቡ ሰዎችንም ሆነ ያላገቡ ሰዎችን ነቃ የሚያደርግ ርዕሰ ጉዳይ ነው። ያገቡ ጥንዶች ተዳራቸውን እንዴት እንደሚመሩ ብቃት የሚጨምርላቸው እውቀትና ክህሎት ለማግኘት ያላገቡ ደግሞ ማንን ላግባ ከሚለው መሠረታዊ ጥያቄያቸው በመነሳትና ለሌሎችም ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ባላቸው መሠረታዊ ፍላጎት ምክንያት የተጻፈን ለማንበብና የሚያወያይም ከተገኘ በድፍረት በውይይቶች ለመሳተፍ ይጓጓሉ።

የሰው ልጅ ምላሹን ለማወቅ ለሚጓጓለት ጥያቄ መሠረታዊ ምላሽ ለመስጠት ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ ያበረከተው መጽሐፍ ጠቀሜታው የጎላ ነው። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳት መጽሐፍትን መሠረት ያደረገ፣ በክሊኒካል እና ክርስቲያናዊ ስነ ልቦና እውቀት፣ ክህሎትና ሳይንሳዊ መርሆዎች የበለጸገ፣ በጸሐፊው የማማከር አገልግሎትና የትዳር ሕይወት ልምድና ምስክርነት የታገዘ መሆኑ እንዲሁም የስነ ጽሑፍ ጥራቱ፣ የሃሳብ ፍሰቱና ግልጽነቱ መጽሐፉን ለየት የሚያደርጉት የመጽሐፉ ጥራቶች ናቸው:: እነዚህ ጥራቶች መጽሐፉ ለአንባቢያን የሚሰጠውን ጠቀሜታም ከፍተኛና ላቅ ያለ እንዲሆን ያደርጉታል::

የትዳር እንቆቅልሽ አካባቢን፣ ዘርን፣ ጥቁርና ነጭ፣ ሀብታምና ድሃ፣ የተማሩና ያልተማሩ፣ መንፈሳዊና ዓለማዊ ... በማለት የሃይማኖት ክፍል ሳይለይ የሰውን ልጆች ሁሉ የሚዳስስ እንቆቅልሽ ነው። እንደሚታወቀው በየትኛውም ማሕበረሰብ ውስጥ አንዱና ዋናው ቀውስ ትዳርና ቤተሰብ ላይ የሚከሰት ከሆነ ሰነባብቷል። በአሁኑ ዘመን ትዳር ለዘለቄታ ሳይሆን የኮንትራት ዓይነት ስምምነት እየሆነ ለመምጣቱ የዓይን ምስክሮች ነን! ትዳርን ለዘለቄታ ብለው በእግዚአብሔርና በቅዱሳን ጉባኤ ወደ ትዳር ዓለም ከገቡበት በኋላ በጥቃቅንና ምናልባትም ለሰው ትልቅ በሚመስሉ ችግሮች ወይንም አለመግባባቶች ምክንያት ክቡር የሆነውን የትዳር ሕይወት እንደቀላል ንደው ሲያፈርሱት መስማትና ማየት የተለመደ ሆኗል። የትዳር መፈራረስ በቤተሰብ፣ በማሕበረሰብና በአገር ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም:: በተለይም በእግዚአብሔር ሕዝብ ማሕበር መካከል የሚያመጣው መንፈሳዊ ዝቅጠት ከፍተኛ ነው። ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ እየሞገተን ያለውም ይህንን ቀውስ ለማስቀረት ልንኖርባቸው የሚገቡንን መርሆዎች እንድንረዳቸው እና እንድንጠቀምባቸው ነው። በየምዕራፉ ያነሳቸው ቁም ነገሮችም በአግባቡ ካልተያዙና መፍትሔ ካልተበጀላቸው ሊያመጡ የሚችሉትን አስከፊ ተጽዕኖ በስፋትና በጥልቀት ከመፍትሔዎቻቸው ጋር በመጽሐፉ አሳይቶናል።

ከፓስተር ሙላቱ በላይነህ ጋር ካለን የረዥም ጊዜ (ከ21 አመት በላይ) ትውውቅና የአብሮነት አገልግሎት በውስጡ ያለውን መንፈሳዊ ቅንዓት ጠንቅቄ እንዳውቀው ዕድል

አግቻለሁ። ለእግዚአብሔር መንግሥት መስፋት፣ ለሰው ልጆች ድነት እንዲሁም
የዳኑትን ደቀ መዝሙር ለማድረግና አማኞችን ለአገልግሎት ለማነሳሳት ያለው ትጋት
ለብዙዎች ምሳሌ የሚያደርገው ነው። ሰዎችን የመስማት አቅሙ፣ ትዕግስቱ፣ ለሰማው
አሳዛኝ ሁኔታ መፍትሔ የመፈለግ ጥበብና ትጋቱ ከዕድሜው ጋር የሚሔድ አልነበረም።
እግዚአብሔር የሩቁን ዘመን ስላየለት ከልጅነቱ **"መፍትሔ"** ፈላጊ አድርጎታል።

እስኪ የመጀመሪያውን መጽሐፍ ርዕስ ላስታውሳችሁ **"የአገልግሎት ተግዳሮቶች እና**
**መፍትሔዎቻቸው" አሁን ደግሞ...** በሰዎች ሕይወት ውስጥ የመግባትና ሸክማቸው
የመካፈል አቅሙን በማሳደግ አሁን ያነሳውን የትዳርን ጉዳይ ትኩረት በመስጠ
መፍትሔ ጠቃሚ የሆነ መጽሐፍ ሲጽፍ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የበቃ እውቀት አለኝ እያለ
አይደለም፡፡ ነገር ግን ይህንን መጽሐፍ እንካችሁ እያለን ያለው ከጌታ የተቀበለው ሸክም
ገና ከልጅነት ዕድሜው ጀምሮ የሰዎችን ስኬታማ ሕይወትና ኑሮ የማየት ጉጉትና ቅንዓ
ያሳደረበትን አደራ ይዞ በመቀጠል የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ከመፈለግ ከመነጩ
ኃላፊነት ነው። ለዚህም እግዚአብሔር በከፈተለት የትምህርት በር በአሜሪካ አገ
የማስተርስ ድግሪውንና ዶክትሬቱን ከሠራ በኋላ እንደገና ትምህርት በመቀጠ
"ክሊኒካል ፓስቶራል ካውንስሊንግ" በማጥናት በማማከር እያገለገለ ይገኛል። ከዚ
እውነታ በመነሳት ነው **"በመጀመሪያው አስርት አመታት በባለትዳሮች መካከል ሊፈጠ**
**የሚችሉ የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው"** በሚል ርዕሰ ጉዳይ የባለትዳሮች
የግጭት መንስኤዎችንና መፍትሔዎቻቸውን በማሳየት በባለትዳሮች መካከል ጤነኛ
ደስተኛ ግንኙነት እንዲኖር ያስተምረናል።

መጋቢ ዶክተር ሙላቱ በላይነህ የግጭት መንስኤዎችን በመዘርዘር ባለትዳሮች ወ
ከፉ ግጭት፣ ፍችና አላስፈላጊ ወደሆኑ ውሳኔዎች ከመግባታችን በፊት ትዳራችን
እንዴት መንከባከብና ለግጭቶቻችንን መፍትሔ መስጠት እንደሚገባን በማሳየ
የከበረውን ትዳር አክብረን እንድንይዝና በትዳር በረከት ተካፋይነታችን ዘላቂ እንዲሆ
ይልቁንም ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎችን በመዘርዘር፣ ከተማረው እና ከልም
ባገኛቸው ዘመን ተሻጋሪ መርሆዎች ይሞግተናል። ጠቢብ ሰው በመጽሐፉ ውስ
በቀረቡት መልካም ምክሮች ይታነጻል፣ በጥልቅ ሃሳቦች አእምሮውን ያንጻል፣ በጠቃ
ከህሎቶች በጋብቻ ውስጥ የሚያጋጥሙትን የሕይወት ችግሮች ይፈታል ከራሱም ባሻገ
ሌሎችን ባለትዳሮች ለመርዳትም ዝግጁ ይሆናል። መልካም ንባብ!

**ወንጌላዊ ዳዊት ቆጢሶ (የነገረ መለኮት አስተማሪ)**



## መግቢያ፡- በዚህ የጋብቻ ዘመን ላይ ማተኮር ያስፈለገበት ምክንያት

1. **ጥንዶች ከግለሰብነት ወደ ባለትዳርነት የተሸጋገሩበትና አዲስ ኑሮ የሚጀምሩበት ወቅት በመሆኑ**

ጥንዶች ከነበራቸው የግልና የቤተሰብ ሕይወት ልምምድ በመውጣት ወደ አዲስ የትዳር ሕይወት ሲገቡ ስለትዳር ካሁን በፊት ከማያውቋቸውና ካልተለማመዷቸው የሕይወት ገጽታዎች ጋር ይጋፈጣሉ። ከአሁን በፊት በእጮኝነት አብረው ሲያሳልፉ በቀጠሮ ተነፋፍቀው ሲገናኙ የነበሩ ሲሆን አሁን ግን በጋራ በአንድ ቤት ጥላ ስር አብረው በመኖር ላይ ናቸው። ይህ የጋብቻ ዘመን ከጫጉላ ወቅት ጀምሮ ቀስ በቀስ በቀጥታ ከሕይወት ተግባራዊ እውነታዎች ጋር የሚጋፈጡበት፣ በእንግድነትና በመጠባበቅ ጭምብል ተደብቆ የነበረው እውነተኛ ማንነታቸው የሚገለጥበትና የተደበቀና ያልታወቀ ባህርያቸው ወደ ተግባር አደባባይ የሚወጣበት ዘመን ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ጥንዶቹ በሚያጋጥሟቸው አዳዲስ ባህሪያትና ድርጊቶች ምክንያት ለግጭት ተጋላጭ የመሆናቸው ዕድል በጣም ከፍተኛ ነው። በዚህ የጋብቻ ዘመን ላይ ማተኮር አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ጥንዶቹ ከግለሰብነት ወደ ባለትዳርነት ሲሸገሩ በሚያጋጥማቸው የአዲስ ማንነት፣ የአዲስ ኑሮና የአዲስ ሕይወት ገጽታ ተደናግጠው ወደ ግጭት እንዳይገቡ ትዳር ማለት ከቀድሞው የግል ዓለማቸው የወጡ አንድ ወንድና አንዲት ሴት (ሁለት ሰዎች) በአንድነት በመጣመር ከሁለቱም ዓለሞችና የሕይወት ልምዶች የተውጣጣና በእግዚአብሔር ቃል የተቀረጸ አንድ የጋራ አዲስ ዓለም የመፍጠር ጋርዮሻዊ የሕይወት ሂደት መሆኑን እንዲረዱ ለማገዝ ነው፡፡

2. **አዳዲስ ልምምዶችና ክስተቶች የሚፈጠሩበትና ለክስተቶች አዲስ የሚሆኑበት ወቅት በመሆኑ**

ይህ የጋብቻ ዘመን ብዙ የተለያዩ አዳዲስ ክስተቶችና ልምምዶች ሊፈጠሩ የሚችሉበት ወቅት ነው። ጥንዶቹ አብረው በመኖር በሚያልፉባቸው ልዩ ልዩ የሕይወት ገጽታዎች ላይ በጋራ መወሰን ይገባቸዋል፡፡ እርግዝና፣ መውለድ፣ ልጆችን ማሳደግ ... የመሳሰሉ ልምምዶች ለቅርብ ጊዜ ተጋቢዎች አዲስ ክስተቶች ናቸው፡፡ የዚህ መጽሐፍ ትኩረት ሁለተኛው ምክንያት በመሆን ሊጠቀስ የሚችለው እነዚህ ልምምዶች ሊፈጥሯቸው የሚችሉ አሉታዊ ተጽዕኖዎችንና አለመግባባቶችን ጥንዶች ከወዲሁ ለመረዳት እንዲችሉና ግጭትን የሚፈቱበት እውቀት፣ ጥበብ፣ ክህሎትና ልምድ ባለመኖሩ የሚፈጠሩ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቆጣጠርና ለማስወገድ እንዲችሉ የሚያግዝ አተዋጽዖ የማበርከት ዓላማው ነው።

### 3. ግጭት የሚበዛበት ይህ የጋብቻ ዘመን ግጭቶችንና የግጭት አፈታት መንገዶች በማወቅ ችግሮችን ለመቀነስ መትጋት የሚያስፈልግበት ወቅት በመሆኑ

ብዙዎቹ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በራሳቸው መንገድ፣ አቀራረብ፣ የጊዜ ገደብ የትምህርት ይዘትና የአሠራር ስርዓት ለማግባት ወስነው ወደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎ ለሚመጡ አባላት እንደ ቤተ ክርስቲያኗ ደንብና መመሪያ ብሎም በወቅቱ እንዳሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መረዳት አንጻር አስፈላጊ የሚሏቸውን መረጃዎች ማስረጃዎች በመሰብሰብና በመጠየቅ ሊጋቡ የተዘጋጁ ወገኖችን እጮኝነት ሲያጸድቁ ሲቀበሏቸው የቅደመ ጋብቻ ትምህርት እንዲማሩ ያደርጋሉ። ትምህርቱም ቅደመ ጋብ ብለን እንጠራዋለን እንጂ ከተጋቡ በኋላ ስለሚገጥማቸው ጉዳይ የሚያነሳ እን ከመጋባታቸው በፊት ምርጫቸውን፣ ውሳኔያቸውን፣ ግምታቸውንና ምክንያታቸው የሚመዝኑበትና ወደ ጋብቻ አንድነት ከመግባታቸው በፊት ሊወስዱት ስለሚገባ እርም የሚጠቁም፣ የሚያስጠነቅቅና የሚያስተምር የትምህርት ይዘትና የጊዜ ሰሌዳ ባለመኖ ከጋብቻ በኋላ የግጭቶችና የፍች ቁጥር እንዲበራከት አስተዋጾ አለው። ይህ መጽሐ የተጻፈበት ሌላው ምክንያት ወደ ትዳር ከገቡ በኋላ ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉ ግጭቶች ለመቀነስና የግጭት አፈታትን ሂደት ለማስተማር ታስቦ ነው።

ይህ ዘመን ግጭትና ፍች የሚበዛበት ወቅት መሆኑን በመጠቆም ከፍተኛ የሀ ትኩረት በመስጠት መልካም የትዳር ግንኙነት መሠረት የመጣልን አስፈላጊነት ይበል ልንረዳው ይገባል። በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠሩና ሊፈጠሩ የሚችሉ ያለመግባባቶች ግጭቶች በከፍተኛ ፐርሰንት የሚታዩትና ብዙ ትዳሮች በፍች የሚበተኑት በዚህ የጋብ ዘመን ክልል ነው:: ለናሙናነት ጥናት ባደረኩባቸውት ሶስት የተለያዩ አጥቢያ አብያ ክርስቲያናት መሪዎችንና የጋብቻ አማካሪዎችን ጠይቄ እንደተረዳሁት በፍች ሂደት ካለ ወገኖች መካከል **ከ75-80%** የሚሆነው ፍች የተመዘገበው በዚህ የጊዜ ክልል ነው:: ይ መረጃ በጠቅላላ ባለትዳሮች መካከል የታየ የፍችን ቁጥር የሚያሳይ ሳይሆን በፍ ሂደት ካለፉ ወገኖች መካከል በዚህ የጋብቻ ዘመን የተፈጸመ ፍችን የሚያሳይ መሆኑ ለመግለጽ እወዳለሁ።[1] ይህም ጥናት በዚህ የጋብቻ ዘመን ውስጥ ያሉ ጥንዶች ከፍተኛ ትኩረትና ድጋፍ የሚያሻው የጋብቻ ዘመን ላይ ያሉ ለመሆኑ አመላካች ነው። ይህ የግጭትና የፍች ቀውስ እንዲቀንስና በተለይ ክርስቲያን ጥንዶች ጤናማና ደስተኛ የሆነ የትዳር ግንኙነትና ቤተሰብ እንዲኖራቸው መሠረት የመጣልን አስፈላጊነት በማሳየት ለዚህ የጋብቻ ዘመን ቤተ ክርስቲያን፣ ተጋቢ ጥንዶች፣ የጋብቻ መምህራንና አማካሪዎች የተለየ ትኩረት መስጠት እንዲችሉ ማሳሰብና ማነሳሳት የዚህ መጽሐፍ መዘጋጀት ሌላኛው አብይ ምክንያት ነው።

[1] ከሶስት የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና የጋብቻ አማካሪዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ የተገኘ መረጃ, ግንቦት 2014.



### 4. ጥንዶችና ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ እንዲችሉ ለማሳሰብ

ይህ የጋብቻ ዘመን በቅርብ የተጋቡ ጥንዶች ለትዳራቸው መሠረት የሚጥሉበትና አዳዲስ ነገሮችን የሚለማመዱበት በመሆኑ ጥንዶችም ሆኑ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ዘመን ልዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል:: የቅድመ ጋብቻ ትምህርትና የማማከር አገልግሎት መስጠት እንዳለበት ሁሉ ቤተ ክርስቲያን በዚህ የጋብቻ ዘመን ላይ የሚገኙ ጥንዶችንም ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት ለማስተማር ትኩረት መስጠትና መዘጋጀት ይኖርባታል:: ቤተ ክርስቲያን በዚህ የዘመን ክልል ውስጥ የሚገኙ ጥንዶችን በማስተማር፣ በመምከርና በትዳር ረጅም ዘመን ከቆዩ በሳል የቤተ ክርስቲያን አባላት ልምድን እንዲካፈሉ በመርዳት በትዳር ሕይወት ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ ቀውሶች እንዲቀንሱና የክርስቶስ መታያ የሆነው የቤተሰብ ተቋም በጽኑ የእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ የትውልድ ማደጊያ እንዲሆን ማነጽ ይጠበቅበታል::

ይህ ተልዕኮ ይፈጸም ዘንድ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ኃላፊነት ለመወጣት አገልግሎት ልዩ ትኩረት እንድትሰጥ መርዳትና በዚህ ዘመን ክልል የሚገኙ ጥንዶች ደግሞ ለመማር ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው መጠቆም ይህንን መጽሐፍ እንድጽፍ ካነሳሱኝ አብይ ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው። የዚህን ዘመን ቀውስ ለመቀነስ ቢቻልም ለማስቀረት የሚደረገው ጥረት መጀመር ያለበት የግድ ሰዎች ወደ ትዳር ከገቡ በኋላ አይደለም:: ቀውሱ ከመፈጠሩ በፊት በዕቅድና በዓላማ በሰዎች ሕይወት ላይ በመሥራት የቀውሱን ስፋትና ፍጥነት በመቀነስ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቆጣጠር ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ይህ መጽሐፍ ከተጻፈባቸው ምክንያቶች አንዱ ይህንን እውነታ በመረዳት ቀውሱን ቀድሞ ለመከላከል እንዲቻል ያላገቡና ሊያገቡ በዝግጅት ላይ ያሉ ወገኖች በቅድመ ጋብቻ የትምህርትና የምክር አገልግሎት ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለመጠቆም ነው።

ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቱን በጠበቀ ትክክለኛ የጋብቻ ምክንያት ወደ ትዳር የሚገቡ ጥንዶች ለጋብቻ ሕይወትና ኃላፊነት ዝግጁ ለመሆን እንዲቀረጹ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባታል:: ትዳር ለመመሥረት የተዘጋጁ ወንድሞችና እህቶችም ከትዳር የሚጠብቁትን የተዛባ ግምት ቀድመው ማስተካከል እንዲችሉ ግንዛቤ ማስጨበጥ ተገቢ ነው:: አዲስ ትዳር መሥራች ወገኖች በጋብቻ ውስጥ ሊገጥሟቸው ስለሚችሉ ተግዳሮቶች በአግባቡ ቀድመው እንዲያስቡና እንዴት ችግሮቻቸውን እየፈቱ የትዳር ግንኙነታቸውን ማጠናከር እንደሚችሉ የእውቀት አድማሳቸውን እንዲያሰፋ ሊረዳ በሚችል መልኩ የቅድመ ጋብቻ ትምህርትና የምክር አገልግሎት ተጠናክሮ ሊሰጣቸው ይገባል:: በዚህ መንገድ አዲስ ትዳር መሥራቾችን በማስተማርና በማዘጋጀት ጤነኛና ደስተኛ የሆነ ግንኙነት ፈጥረው በትዳር ውስጥ ያለው በረከት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቤተ ክርስቲያን መርዳት እንዳለባት ማሳሰብም ከዚህ መጽሐፍ ትኩረቶች አንዱ ነው።

የትምህርትና የምክር አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መርህ መሠረት በማድረ ግለሰቦች፣ ባለትዳሮች፣ ቤተሰብና ቤተ ክርስቲያን የዘመኑን ተግዳሮቶችን በጽድ መርህ እንዲያሸንፉ መርዳት ላይ ያነጣጠረ መሆን አለበት፡፡ ተግባራዊ የሆነ የጋብ ትምህርትና የምክር አገልግሎት በዚህ ዘመን ከመቼውም ዘመን በበለጠ በቂ ጊ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ለተጋቢዎችና ለባለትዳሮች የሚያስፈልግና የሚመጥን ትምህርት ምክር በትክክለኛ አገልጋዮች እንዲሰጥ በማድረግ ግጭትን፣ መለያየትንና ፍች ለመቀነስ ጥረት የማድረጉ ሥራም ከመቼውም ጊዜ በላይ አጽንዖት ተሰጥቶት መተግበ ያለበት ባለንበት ዘመን ነው።

**ፓስተር ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ**
**ግንቦት 05, 2007 ዓ.ም**
**Pastor Dr. Mulatu Belayneh, licensed Clinical Pastorlal Counselour-Advanced Certified (LCPC)**
**May 13, 2015**

# ክፍል አንድ(1)፡- የጋብቻ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

# ምዕራፍ አንድ(1)
# የጋብቻ ትርጉምና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች

## 1. የጋብቻ ምንነት

ከሁሉ በፊት የጋብቻን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንነት መረዳት አስፈላጊ ነው። ጋብቻ የመሠረተው እራሱ እግዚአብሔር ነው። ጋብቻ ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊ እግዚአብሔር የሰውን ብቸኝነት በማየትና በማሰብ የሰውን ልጅ አካላዊ፣ ግብረ ስጋ መንፈሳዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ ስሜታዊና ማሕበራዊ ፍላጎት ለማርካት ለሰው ልጆች ጥቅ በኤደን ገነት የመሠረተው ተቋም ነው።

ጋብቻ በሁለት ተቃራኒ ጾታዎች መካከል በእውነተኛ ፍቅር በመተሳሰብ በመፈላለግ የሚጀመር ሁለቱ ጥንዶች በእግዚአብሔር ፊት ቃል ኪዳን በማድረ የሚስማሙትና የሚኖሩት ቃል ኪዳናዊ ትሥሥር ነው። ሁለቱ ተቃራኒ ጾታዎ በእግዚአብሔር፣ እንደ ጥንዶቹ ፣ እንደ አገሩና አካባቢው ሁኔታ ደግሞ በበ ክርስቲያንና በሰዎች ፊት ሕጋዊ በሆነ መንገድ ቃል ኪዳን በመፈጸምና በመፈራረም ወ ጋብቻ ኪዳናዊ ጥምረት የሚገቡበትና የሚኖሩበት ተቋም ነው።

ይህን ተቋም መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነው ኪዳናዊ ኅብረት ውስጥ በመግ የመሠረቱት ጥንዶች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱሳዊው የተቋሙ መርህ መሠረት ዘመናቸው የመምራትና የመኖር ኃላፊነት አለባቸው:: እግዚአብሔር *"እናንተም። ስለ ምንድር ነ ብላችኋል። ሚስትህ ባልንጀራህና የቃል ኪዳንህ ሚስት ሆና ሳለች አርስዋን አታልለሃታልና እግዚአብ በአንተና በልጅነት ሚስትህ መካከል ምስክር ስለ ሆነ ነው። እግዚአብሔር የሕይወትን መንፈስ አ አድርጎ ጠብቆልን የለምን? እርሱም የሚፈልገው ምንድር ነው? ዘር አይደለምን? ስለዚህ መንፈሳች ጠብቁ፥ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል።"* /ሚል 2: 14-15/ በማለት የተቋሙን መር የጣሱትን ሰዎች የገሰጸበት እውነት ግልጥ በሆነና በተቋሙ መርህ መሠረት የመና ጉዳይ የሰዎች ፍላጎት የሚለዋወጠው ሳይሆን በእግዚአብሔር የተደነገገ ሕግ መሆነ ያሳያል::

በዚህ የጋብቻ ትርጉም ውስጥ በተለይ ባለንበት ዘመን ልዩ ትኩረት ሊሰጠ የሚገባው አሳብ ጋብቻ የሕይወት ዘመን ቃል ኪዳናዊ ትስስር የመሆኑ እውነታ ነው፡ ከዚህ እውነታ ጋር መግባባት እንድንችል ለአንድ አፍታ ቃል ኪዳን ማለት ምን ማለ እንደሆነ በአጭሩ እንቃኛለን::

**የቃል ኪዳን ምንነት፡-** ቃል ኪዳን በሁለት ሰዎች፣ ቡድኖች፣ ጥንዶችና ፓርቲዎ መካከል የሚደረግ ውል ወይም ስምምነት ነው። በማንኛውም ቃል ኪዳን ውስጥ የቃ ኪዳን ሰጪ፣ ተቀባይ፣ የአቀባበል ምልክት፣ ተስፋና የተስፋውም ምልክት ይገኛሉ፡

[2] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር. <u>የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት</u>, አዲስ አበ በባናዊ ማተሚያ ቤት ታተመ 1992 ዓ.ም ገጽ 92.





ክርስቲያናዊ ጋብቻ የዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን እንጅ የኮንትራት ውል አይደለም:: የክርስቲያናዊ ጋብቻን በዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን ላይ የተመሠረተ መሆን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ያሳያል /ዘፍ 2: 18-24፣ ማቴ 19: 4-6፣ ማር 10: 7-9 ና 1ኛ ቆሮ 7: 8/:: እግዚአብሔር ጋብቻን ለሰው ልጆች የሰጠው የዕድሜ ልክ በሆነ ቃል ኪዳን ነው። ስለዚህ ጋብቻ የኮንትራት ውል ሳይሆን የዕድሜ ልክ ቃል-ኪዳን ነው:: *"... ስለዚህ ሰው አባቱን እና እናቱን ይተዋል በሚስቱ ይጣበቃል..."* /ዘፍ 2: 18-24፣ ማቴ 19: 4-6/ በእድሜ ልክ ቃል ኪዳንና በኮንትራት ውል መካከል ከፍተኛ የሆነ ልዩነት አለ።

**የመጀመሪያው** ልዩነት የጊዜ ገደባቸው የተለያየ መሆኑ ነው። በዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን የተመሠረተ ጋብቻ ለዕድሜ ልክ መቀጠል ያለበት ሲሆን በኮንትራንት ውል የተመሠረተ ጥምረት ግን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚቆይ ነው።

**ሁለተኛው** ልዩነት ደግሞ በዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን የተመሠረተ ጋብቻ ሁለንተናን ለሌላው አካል እስከ ሞት ድርስ የመስጠት ሂደት መሆኑ ነው። በዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን የታሰረ ጋብቻ በሞት ካልሆነ በቀር በማንኛውም ቅድመ-ሁኔታ መፍረስ የማይችልበት ስምምነት ላይ ያረፈ ሲሆን የኮንትራት ቃል ኪዳን ግን ስምምነቱ ለአንዱ አካል ካልተመቸው፣ ካልጠቀመው ወይም አንዱ አካል ካልፈለገው የማይቀጥል በሁኔታ ላይ የተመሠረተ ውል ነው። *"...ሴት ባልዋ በሕይወት ሳለ የታሰረች ናት፤ ባልዋ ቢሞት ግን በጌታ ይሁን እንጂ የወደደችውን ሊታገባ ነጻነት አላት።"* /1ኛቆሮ 7: 39/

**ሶስተኛው** ልዩነት በዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን የታሰረ ጋብቻ እንደ እግዚአብሔር ቃል በክርስቲያናዊ ባህርይ መርህ መሠረት ይቅርታ በመስጠትና በመቀበል ተማምኖ ያለስጋት በመኖር ለመቀጠል የሚጥር ሲሆን ኮንትራት የሆነ ጋብቻ ግን ከእግዚአብሔር ቃል መርህ በተቃራኒ ውጫዊ ጥቅሞችን ማግኘትን ዓላማ በማድረግ በፍርድ ቤቶችና ሌሎች ተመሳሳይ በሆኑ ድርጅቶች ማዕከላዊነት የሚጀመርና በእነዚሁ ተቋማት ዳኝነት ብቻ የሚያልቅ ስምምነት ነው። ክርስቲያኖች ወደ ጋብቻ በሚገቡበት ወቅት ሊያስቡበትና ሊያተኩሩ የሚገባቸው የእግዚአብሔር ቃል መመሪያ እና የውስጥ ውበት (ባህርይ) ላይ እንጂ ውጫዊ በሆኑ ነገሮች ላይ እንዳይሆን የሚመከረው ጋብቻቸው ጊዜያዊ እንዳይሆን ነው።

በዕድሜ ልካዊ ቃል ኪዳን ጋብቻና በኮንትራት ጋብቻ መካከል ያለው **ሌላው ልዩነት** የመጀመሪያው በልብ መሰበር፣ በመሰጠትና ከልብ በሆነ ፈቃድ ቃል ኪዳኑን መፈጸም ላይ ሁለተኛው ግን ሁልጊዜ ከልብ ይልቅ በስምና በፊርማ ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው። ይህን የምንለው ለዕድሜ ልክ የሚጸና ቃል ኪዳናዊ ትሥሥር ስምና ፊርማ አያስፈልገውም ለማለት ሳይሆን ከልብ የጀመረና ጥንዶቹ በልብ ጥምረት የመሠረቱት

ክርስቲያናዊ ጋብቻ ብቻ እስከ ሞት የሚዘልቅና ከስምና ከፊርማ በላይ የሆነ ት
ዓላማ ያለው መሆኑን ለማስጨበጥ ነው።

**የመጨረሻው** ልዩነት እንደ እግዚአብሔር ቃል በዕድሜ ልክ ቃል ከ
የተመሠረተ ጋብቻ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ እውነተኛ በሆነ ፍቅር ራስንና ያለውን
ሁሉ ለሌላው መስጠት ላይ ሲያተኩር በኮንትራት ውል ላይ የተመሠረተ ጋብቻ
ከመስጠት ይልቅ መቀበል፣ ከመጥቀም ይልቅ በሌላው መጠቀምንና ከማካፈል ይ
በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከሌላው ወገን የሚገኘውን ጥቅማ ጥቅም መሰብሰብ
የሚያተኩር ስምምነት ነው። በክርስቲያናዊው ቃል ኪዳን ላይ የተመሠረተ ጋ
ሁለንተናዊ የሆነ መስጠትን የሚጠይቅና በተለያዩ የሕይወት ገጠመኞች ማለ
በጤንነትና በሕመም፣ በማግኘትና በማጣት፣ በደስታና በሐዘን፣ በመልካም ገ
በመጥፎ ወቅት አብሮ ተፈቃቅሮና ተደጋግፎ በታማኝነት እስከ ሞት ድረስ የመዘ
መርህ መሠረት ያደረገ ስምምነት ነው።

**በሚከተለው ሰንጠረዥ የቀረበው ንጽጽር ከላይ የተገለጠውን እውነት በአ
ለማጤን ያስችላል፡-**

| ተ.ቁ | በኮንትራት ውል ላይ የተመሠረተ ጋብቻ፡- | በዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን ላይ የተመሠረተ ጋብቻ፡- |
|---|---|---|
| 1 | ዓለማዊ ነው | ክርስቲያናዊ ነው |
| 2 | ጊዜያዊ ነው፡- በውሉ ላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ብቻ የፀና ይሆናል | የዕድሜ ልክ ጥምረት ነው |
| 3 | ስምምነቱ አንዱ አካል እስካልተመቸው ድረስ የሚቀጥልና የሚፈርስ ነው። | እስከ ሞት ድረስ የሚቀጥል ነው። |
| 4 | በፍርድ ቤቶች፣ በተለያዩ ድርጅቶች ላይ ብቻ የሚያተኩር ውል ነው | በእግዚአብሔር ማዕከልነት በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ብቻ የሚደረግና የውል ገቢዎችን ባህርይ፣ ሕይወትና የታመነ ማንነትን የሚጠይቅ ነው። |
| 5 | በስምና በፊርማ ብቻ የሚከናወን ነው | የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት በማድረግ በተሰበረ ልብ፣ በተሰጠ ማንነት የሚከናወን ነ |
| 6 | በዋናነት በሌላው ሰው ለመጠቀም በመፈለግ ላይ ያተኮረ፣ የራስን ፍላጎት ብቻ ማስከበርን ዓላማው ያደረገ ነው፡፡ | ሌላውን መጥቀም፣ ለሌላው አካል መኖርና ራ ለሌላ ሰው ጥቅም መስጠትን መሠረት ያደረገ ክርስቶስን ማክበርን ዓላማው ያደረገ ነው፡፡ |

ሠንጠረዥ 1፡1





## II. ጋብቻ ለሰው ልጆች የተሰጠበት ዓላማ

### 1. አጋርነት

ጋብቻ *"ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም"* /ዘፍ 2፡ 20/ በሚለው ቃሉ መሠረት የአዳምን ብቸኝነት ለማስወገድ ለሰው የሚያስፈልገውን ሙላት ከመልካምነቱ በሚያዘጋጀው በእግዚአብሔር ለሰው ጥቅም የተመሠረተ ተቋም ነው። የአዳምን ብቸኝነት በማስወገድና ረዳት በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ *"እንደ እርሱ ዓይነት ረዳት አልተገኘለትም"* /ዘፍ 2፡20/ በማለት አዳም ረዳት እንደሚያስፈልገው እግዚአብሔር ራሱ ግልጥ አድርጓል፡፡ ስለዚህ የሰው ፍላጎት እንደ እርሱ ያለች ሰውና ተቃራኒ ጾታ የሆነችን አጋር ሴትን እግዚአብሔር ለአዳም በማዘጋጀቱ በእግዚአብሔር አሠራር ሊሟላ የቻለ መሆኑን በዘፍጥረት ሁለት ከተጠቀሰው ቃል ማየት ይቻላል። ጋብቻ የአዳምና የሔዋን አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ መንፈሳዊ፣ ስነ ልቦናዊና ማሕበራዊ ፍላጎት በአብሮነታቸው እንዲሟላ የተቋቋመ ነው፡፡ ጋብቻ ሁለቱ ጥንዶች ሁለንተናዊ መደጋገፍን አንዳቸው ለሌላቸው በመስጠታቸው እርስ በእርስ መሟላትን ማግኘት የሚችሉበት ቃል ኪዳናዊ ትሥሥር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንደሚል *"አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል"* /መክ 4፡ 9/፡፡

የጋብቻ ኅብረት በጥንዶች የጠለቀ ግንኙነት በምንምና በማንም ሊሞላ የማይችልን ክፍተት ለመሙላትና ለማርካት አንዱ ለሌላው ረዳት በመሆን ተስማምቶ የሚኖርበት ኪዳን ነው። በጋብቻ ውስጥ ያለውና በጥንዶቹ መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት ከሌሎች ግንኙነቶች ይልቅ የተለየና የጠለቀ አንድነት ነው። ይህም አንድ ወንድና አንዲት ሴት ወደ ጠለቀ የግንኙነት አንድነት ደረጃ በመድረስ የእግዚአብሔርን ዓላማ በሕይወታቸው በጋራ በመደጋገፍ ለማከናወን ያስችላቸዋል።

### 2. ለጥንዶቹ የጋራ ደስታ

ጋብቻ የተሰጠበት አንዱ ዓላማ ለጥንዶቹ የእርስ በእርስ ደስታ መፍጠርና የተፈጠረውን ደስታ መጠበቅ ነው። *"ምንጭህ ቡሩክ ይሁን ከጉብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ።"* /ምሳሌ 5፡ 18/ ብሎ በመናገር መጽሐፍ ቅዱስም ይህንን እውነት ይመሰክራል፡፡ በጋብቻ ውስጥ ያለውን የእርስ በርስ ደስታ ለመፍጠርና ለመጠበቅ እንደ ባለትዳር ጥንዶቹ እርስ በርስ መዋደድ፣ አንዱ የሌላውን ስሜት መጠበቅ፣ በየጊዜው ይቅርታን መለማመድ፣ የሌላውን አካል ፍላጎትና ስሜት መረዳትና መረዳዳት፣ በግብረ ስጋ ግንኙነት አንዱ ሌላውን ሳይከለክልና የሌላውን አጋር ስሜት ለማርካት ጥረት በማድረግ በብዙ አቅጣጫ በመደጋገፍ አብረው መኖር ይጠበቅባቸዋል።

### 3. የሰውን ዘር መተካት (ወላጅነት)

እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠር ጅማሬ ላይ ከተናገራቸውና ከሰጣቸው በረከቶች አንዱ በጋብቻ ውስጥ ልጅ የመወለድና ዘርን የመተካት በረከት ነው፡፡ እግዚአብሔር ለወላጆች ልጆችን በመስጠት ቤተሰብ እንዲመሠረት እንደ ፈለገ ቃሉ እንዲህ ሲል

ይገልጽልናል:- *"እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው:- ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት.* /ዘፍ 1: 28/:: ይህ አሳብ ከጋብቻ ውጭ ልጅ አይወለድም ወይም ዘር አይተካም ወደ የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል:: አዎ ከጋብቻ ውጭ በሚደረግ ግንኙነት ልጅ ሊወለ ይችላል:: ከጋብቻ ውጭ የሚወለድ ልጅ ግን እርሱ ራሱ ያጠፋው ጥፋት ባይኖር፣ እንኳን በጤናማ ጋብቻ ላይ በተመሠረተ ኅብረት ውስጥ የሚገኘውን የተሟላ ፍቅ( እንክብካቤና ጥበቃ በማጣት በቀውስ ውስጥ የሚወድቅ ይሆናል:: በወላጆቹ ጥፋ ምክንያት ባልበደለው በደል ይሰቃያል:: ለወላጆቹም የደስታ ምክንያት ሳይሆን የጠ( የንትርክና የሰላም ማጣት ምክንያት ይሆናል:: ነገር ግን ልጆች ከመጀመሪያ( የእግዚአብሔር ቃል ግልጥ እንዳደረገው በሁለት ተቃራኒ ጥንዶች የጋብቻ ጥምረ ውስጥ እግዚአብሔር ለወላጆች የሚሰጣቸው ስጦታዎች ናቸው። ከጋብቻ ው የሚደረገውን ማንኛውንም የግብረ ስጋ ግንኙነት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ዝሙት ብ የሚጠራው ሲሆን ዝሙትም በእግዚአብሔር ቃል በግልጥ የተወገዘ ነው።

## 4. በጋራ ወደ ፍጹምነት እንዲያድጉ

ጥንዶቹ እርስ በርሳቸው መረዳዳት እንዲችሉ ለሰዎች የተሰጠ የመጀመሪያ ተቋ ጋብቻ ነው። ሁለት ተቃራኒ ጾታ ያላቸው ሰዎች እርስ በእርስ ተፈላልገውና ተዋደ ወደ ጋብቻ የሚገቡት በአንዱ ብርታት ሌላው እንዲደገፍና እርስ በእርስ በመሳሳል ( ፍጹምነት በማደግ የክርስቶስን መልክ እንዲመስሉ ነው። ፍጹም የሆኑ ጥንዶችና ፍጹ የሆነ ትዳር ሊኖር አይችልም። ስለዚህ ባለትዳሮች ጉድለትና ድካም ያለባቸው ሰ( በመሆናቸው በጋራ እየተረዳዱ፣ በየጊዜው በማደግና በመለወጥ ወደ ፍጹም ለመድረስ ሁልጊዜ በግስጋሴ ላይ ያሉ መሆናቸውን እያሰቡ በትዕግስት አብረው መ( አለባቸው። ይህ ሲሆን *"ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸ( የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወሰናቸና፤"* /ሮሜ 8: 29/ የሚለው አምላካዊ ቃ በህያውነት በግል ሕይወታቸው፣ በሕብረታቸውና በቤታቸው ውስጥ በሙላት መፈጸ ይቀጥላል::

## III. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጋብቻ መርህ

### 1. **መተው፡-** *"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል"* /ዘፍ 2: 24/

እግዚአብሔር ጋብቻን ለሰው በሚሰጥበት ወቅት ወደ ጋብቻ የሚገቡ ጥንዶ መተግበር ያለባቸው የመጀመሪያው መርህና እርምጃ መተው በሚለው ቃል ተገልጧል ይህ ቃል ተጋቢዎች ወደ ትዳር ከገቡ በኋላ ቀድሞ እንደ ነበረው ከወላጅ አስተዳደር ስልጣን ሥር መሆንን ማቆምና ማቋረጥ ያለባቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው። ሰ( አባቱንና እናቱን ይተዋል ሲባል ትዳር የሚመሠርቱ ሰዎች ፈጽሞ ከወላጆቻቸው ጋ ያላቸውን የወላጅነትና የልጅነት ግንኙነትን ማቋረጥና መረዳዳትንና መቀራረብን መጣ( አለባቸው ማለት አይደለም። ነገር ግን የመተው መርህ ቀድሞ ከወላጅ ጋር የነበረው





ጠንካራ ግንኙነት በማላላት ከትዳር አጋር ጋር ወደ ሚደረግ ጥብቅና በጣም ቅርብ የሆነ ጥምረት ወደ መግባት የመሸጋገርን አስፈላጊነት የሚያመለክት መርህ ነው።

በሌላ አገላለጥ ለማብራራት የወላጆችን ቤት እንደ አንድ ትንሽ መንግሥት ማየት ብንችል፡ መተው የሚለው ቃል አዲሶቹ ተጋቢዎች ከዚህ ትንሽ መንግሥት አገዛዝ ስርዓት ተመርቀው በመውጣት ራሱን ችሎ የሚተዳደርና የራሱ የአስተዳደር ስርአት ያለው አዲስ ቤተሰብ ወይም የራሳቸውን ትንሽ መንግሥት መመሥረታቸውን የሚያሳይ ነው:: ሁለቱ ቤተሰቦች አዲሶቹ ጥንዶች ከተጋቡበት ዕለት ጀምሮ ሁለት ራሳቸውን የቻሉ ትናንሽ መንግሥታት ናቸው:: ከዚህ በኋላ አንደኛው መንግሥት በሌላኛው መንግሥት ስርአት ውስጥ የሚኖርበት ምንም ዓይነት የተፈቀደ ሕግ የለም:: ነገር ግን የትብብርና ጠቃሚ መርሆዎችን የመማማር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የመለዋወጥ ሕብረታቸው ሳያቋረጥ ሊቀጥል ይገባል::

### 2. **መጣበቅ፡-** *"... በሚስቱም ይጣበቃል"* /ዘፍ 2: 24/

ጋብቻ አባትንና እናትን በመተው ውሳኔ የሚጀምርና በፈቃደኝነት በማንኛውም ሁኔታ በማይለዋወጥና ታማኝነት በተሞላው ማንነት ለትዳር አጋር ራስን መስጠት ነው። መጣበቅ የሚለው አሳብ ይህንን እውነታ የሚያሳይ ነው:: መጣበቅ ያልቻሉ ጥንዶች በአስቸጋሪ ወቅት አብረው ለመቀጠል ሊቸገሩና ለመለያየት ሊፈጥኑ ይችላሉ። መጣበቅ ሲኖር በሕመምና በጤንነት፣ በማጣትና በማግኘት፣ በሐዘንና በደስታ ... የማይለዋወጥና ተፈትኖ የማይወድቅ ታማኝ ባልና ሚስት መሆን ይቻላል። እውነተኛ የሆነ መጣበቅ ከሌለ ማጣትና መከራ ብቻ ሳይሆን በአግባብ ያልተያዘ ምቾት ወይም ደስታና ስኬት እንኳን የጋብቻ መሠረታዊ ችግር ወደ መሆን ይመጣል:: በጊዜ ካልተስተካከለም ችግሩ አድጎ በዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን የተሳሰሩ ጥንዶችን ውል በተቃወሰ መንገድ እንዲፈርስ ሊያደርግና የጥንዶችን አብሮነት ሊለያይ ይችላል ።

### 3. **አንድ ስጋ መሆን፡-** *"... ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።"* /ዘፍ 2: 24/

አንድ ስጋ መሆን የሚለው መርህ በዋናነት በጥንዶቹ መካከል ያለውን የግብረ ስጋ ግንኙነት አንድነት የሚያሳይ ነው። ጥንዶቹ አንዱ የሌላውን የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት የማርካት ኃላፊነት አለባቸው:: በጋብቻ ውስጥ ተጋቢዎቹ አንድ ከሚሆኑበት መንገድ አንዱ የግብረ ስጋ ግንኙነት ነው። ይህን አንድነት አንዱ የሌላውን ስሜትና ፍላጎት በመረዳት፣ በመጠበቅና በማርካት ሊጠብቁት እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ ይመክራል። *"ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ። ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ። ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፤ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ።"* /1ኛቆሮ 7:3-5/

### 4. ግልጥነትና የጠለቀ ግንኙነት መኖር፡- *"አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ አይተፋፈሩም ነበር።" /ዘፍ 2፡ 25/*

በሰዎች መካከል ፍጹም ግልጥነትና የጠለቀ ግንኙነት ሊኖር የሚችለው በጋብ ተቋም ውስጥ ነው። የግንኙነቱን ጠንካራነት የሚያመለክተን አባትንና እናትን በመተወ ከሚስት ጋር በመጣበቅና አንድ ስጋ በመሆን የተመሠረተ ግንኙነት መሆኑ ነው በእንደዚህ ዓይነት ጠንካራ መሠረት ላይ ባረፈ የትዳር ግንኙነት ውስጥ በተጣመ ጥንዶች ኅብረት የሚያሳፍርና ነጻነት የሚነፍግ ግንኙነት ሊኖር አይችልም። አዳም ሔዋን ሁለቱም ዕራቁታቸውን በነበሩበት ጊዜ እንኳን በመካከላቸው መተፋፈ እንዳልነበረ ቃለ እግዚአብሔር ይነግረናል። ለጤነኛና ለደስተኛ የትዳር ሕይወ መፈጠር ጥንዶቹ በመካከላቸው የጋራ የሆነ ነፃ ስሜት፣ ሃሳብ፣ ፍላጎትን የመግለ መቀባበል፣ የመረዳትና ብሎም የመረዳዳት ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል።

## IV. ጋብቻ የሚጠይቀው የግል ኃላፊነትና ተጠያቂነት

### 1. የባልና የሚስት ድርሻ

ጋብቻ ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሞላበት ተቋም ነው። እግዚአብሔር ጋብቻን ለሰ ልጆች ሲሰጥ አብሮ የመኖርን የባልና የሚስት ኃላፊነትና ተጠያቂነት መመሪያ ጭም ሰጥቷል። ባልና ሚስት ይህን ኃላፊነት የተረዱ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ይህንን ኃላፊ በአግባቡ ካልተረዱና ሊወጡትም የማይችሉ ከሆነ ትዳራቸው ቀውስ ውስጥ መግ አይቀሬ ነው። በግልጥ ኃላፊነት ያልታወቀበት የትዳር ግንኙነት ደግሞ ምን ሊ እንደሚችል መገመት አያዳግትም። እንደሚገባ እንዳይግባቡና ግጭት እንዲበዛ ብሎ ለመለያየት ቅርብ የሆኑ ጥንዶች ሊያደርጋቸው ይችላል።

በጋብቻ ውስጥ ግልጥ የሆነ የግል ኃላፊነትን አለመረዳት ብቻ ሳይሆን ኃላፊነ ተረድቶ በሚገባ አለመወጣት በአሁኑ ዘመን የብዙ ክርስቲያን ባለትዳሮች ችግር ነወ ይህንን ችግር መቀነስ ከተቻለም ከችግሩ ሙሉ በሙሉ መውጫ መንገዱ መጽሐ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ የሚያስተምረውን መስማትና ሕይወትን በእግዚአብሔር ቃ እውነት መምራት ነው፡፡ ችግሩ ብዙ ባለትዳሮች ከዚህ እውነት ጋር መግባባ አለመቻላቸው ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን የትዳር መመሪያቸው ለማድረግ የሚጥ ጥንዶች ደግሞ ተገቢ ባልሆነና በተሳሳተ መንገድ ቅዱሱን መጽሐፍ በመተርጎ ይስታሉ፡፡ ስለዚህ የትዳር መመሪያ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን ጥንዶቹ በራሳቸ ባህል፣ መነጽርና ፍላጎት መተርጎምንና መጥቀስን በመተው ሙሉ አሳቡን እንደሚገ ማንበብ፣ ማጥናት፣ ከሌሎች አስተማሪዎች መስማት፣ ማሰላሰልና መታዘ ይኖርባቸዋል። ለቃሉ ስፍራ የሚሰጡ፣ ቃሉን በሙሉ አሳቡ የሚረዱ፣ ለመስማ ፈቃደኛ የሆኑና ለመታዘዝ የተዘጋጁ ባለትዳሮች ግንኙነታቸው፣ ውሳኔያቸው ተግባቦታቸው መልካምና ጤናማ ይሆናል። እነዚህ ባለትዳሮች በጋብቻ ውስጥ





የየራሳቸውን ኃላፊነትና ሚና በሚገባ ይረዳሉ፡፡ ድርሻቸውን ለመወጣትም ዝግጁ ናቸው፡፡

### 2. ከግል ድርሻ ላይ ትኩረት ማድረግ

መጽሐፍ ቅዱስ የባለትዳሮችን ኃላፊነት ከመግለጽ ባሻገር በእያንዳንዳቸው የግል ኃላፊነት ላይ እንዲያተኩሩ በግልጥ ይመክራል። መጽሐፍ ቅዱስ ባለትዳሮችን የሚያስተምረው ቃሉን እየጠቀሱ መብታቸውን እንዲያስከብሩ ሳይሆን እውነቱን እየጠቀሱ እንዲታዘዙና ከግል የሥራ ድርሻና ተጠያቂነት ላይ እንዲያተኩሩ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ባል ሚስቱን ይውደድ፣ ይንከባከብ፣ ይመግብ፣ ይምራ፣ ይጠንቀቅና የሚያስፈልጋትን ያድርግላት የሚሉ ኃላፊነቶችን እና ሚስትን በሚመለከት ደግሞ ለባሏ ትገዛ፣ ትታዘዝና አትከላከሉ የሚሉ በውስጣቸው ዝርዝርና ሰፊ ዋና ዋና ቁም ነገሮች ያሉባቸውን መርሆዎች የያዘ መልዕክት ነው። በባለትዳሮች መካከል አለመግባባት፣ ግጭትና መለያየት እንዳይፈጠር ካስፈለገ ጥንዶቹ የየግል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኃላፊነታቸው ላይ ማተኮርና ኃላፊነታቸውን ለመወጣትም ጥረት ማድርግ ይጠበቅባቸዋል። ጥንዶቹ የየግል የሥራ ኃላፊነታቸው ላይ ማተኮርና መታዘዝ ያለባቸው ምርጫ ስለሌላቸውና በሌላቸው ወቅት ሳይሆን በብዙ ምርጫዎች መካከል እውነተኛ የሆነ መታዘዝን ማሳየትና ለጋራ የትዳር ሕይወት የየበኩላቸውን ኃላፊነት መወጣታቸው ተገቢ ስለሆነ ነው።

**ክርስቲያናዊ ጋብቻ የእግዚአብሔርን ቃል እየጠቀስን መብታችን የምናስከብርበት ሳይሆን የቃሉን እውነት እየጠቀስን የምንታዘዝበት ተቋም ነው።**

## V. የጋብቻ አጠቃላይ ባህሪይ (ተፈጥሮ)

ጋብቻ ለማንኛውም ሕብረተሰብ ማዕከላዊና ማሕበራዊ መሠረት መሆኑን ከፍጥረት መጀመሪያና ከምንኖርበት ከግዝፈተ ዓለም ነባራዊ ሁኔታ መረዳት ይቻላል። መልካም ትዳር ለመልካም ቤተሰብ መሠረት ነው። መልካም ቤተሰብ ለመልካም ቤተ ክርስቲያን መሠረት ነው፡፡ መልካም ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ለመልካም ሕብረተሰብ መሠረት መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። እግዚአብሔር ገና ከጥንት ፍጥረተ ዓለሙን ሲፈጥር ሕብረተሰብን ሳይሆን ጥንዶችን ባልና ሚስቶች አዳምንና ሔዋንን ብቻ በመፍጠር ማሕበረሰብ ሁሉ ከእነርሱ እንዲገኝ ማድረጉ የዚህ እውነታ ማሳያ ነው፡፡ በማንኛውም ሕብረተሰብ ዘንድ በቋሚነት የሚታይ አለማቀፋዊ ባህልና ልማድ ቢኖር ጋብቻ የተባለው ተቋም ነው። ዛሬ በተለያየ መንገድ የመጀመሪያውን የእግዚአብሔርን ሃሳብ የሚቃረንና ለማፍረስ የሚጥር ብዙ ልምምድ ቢታይና ተግዳሮት ቢፈጠርም ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል በዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን የሚታሰር የጠለቀ ግንኙነት መሆኑ ግን የታወቀና ሊለወጥ የማይገባው አምላካዊ ሕግ ነው።

በጋብቻ ውስጥ ያለውን ግንኙነት ከሌሎች ማሕበራዊ ግንኙነቶች የተለ
የሚያደርገው የጠለቀና የጠበቀ አንድነት የሚገለጽበት ተቋም በመሆን መመሥረ
ነው። መጽሐፍ ቅዱስ *"... በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ"* /ዘፍ 2፡ 2
በሚለው መርህ ግልጥ ያደረገው ይህንን እውነት ነው። የሰውን ውስጣዊ የጠለ
ግንኙነት ለማርካት የተፈጠረ ማሕበራዊ ተቋም ቢኖር ጋብቻ ብቻ ነው የምንለው
ለዚህ ነው። ሌላው የጋብቻ ልዩ ባህርይ ልጆችን በአስተማማኝ፣ ጤናማና ውጤታ
በሆነ መንገድ ለማሳደግ ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑ ነው። ከወላጆቻቸው ጋር ካደ
ልጆች ይልቅ በወላጅ እጅ ያላደጉ ልጆች አካላዊ፣ ስነ ልቦናዊና መንፈሳዊ ጤንነታቸ
ለቀውስ ተጋላጭ ነው። በዚህ ችግር ውስጥ የወደቁ ልጆች ሁለንተናዊ ማንነታቸው ላ
የተረጋጋና ምቹ ሁኔታ ሊኖራቸው ስለማይችል ሁለንተናዊ ቀውስ ያጋጥማቸዋል
በትምህርት ውጤታቸውም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ቀጣይ ለሆነ ከፍተ
ትምህርት እንዳይደርሱና ቢደርሱም የጀመሩትን እንዳይፈጽሙ ሊያደርጋቸው
ይችላል። በአካዳሚ ውጤታቸው ብቻ ሳይሆን ብቸኝነት፣ ገለልተኛነት ብሉ
በማሕበራዊ ኑሯቸው ላይ የግንኙነትና የግለኝነት ችግርም ሊያጋጥማቸው ይችላል።

## VI. የጋብቻ የላቀ ምሳሌነት

### 1. በእግዚአብሔርና በእስራኤል ሕዝብ መካከል ለነበረው ኅብረት ያለ ምሳሌነት

ጋብቻ ምሳሌነቱ ላቅ ያለ ነው፡፡ በዘመነ ብሉይ ቅዱሳት መጽሐፍት እንደሚናገ
እግዚአብሔር እንደ ባልና የእስራኤል ሕዝብ እንደ ሚስት በምሳሌ ተጠቅሰዋል። በባ
በሚስት መካከል ያለውን የቀረበና የጠለቀ የፍቅር ግንኙነት ወይም በጋብቻ ው
ያለውን ችግር ምሳሌ በማድረግ እግዚአብሔር በእርሱና በእስራኤል ሕዝብ መካ
ያለውን ኅብረት ለመግለጥ ተጠቅሞበታል፡፡ አምላክ ሁኖ እያለ ለሕዝቡ፣ በተ
ኃጢአት ውስጥም ለሚመላለሱ እንደገና ዕድል በመስጠት አምላካቸውና አባታቸ
በመሆን ሊቀርባቸው ብሎም ከጠላቶቻቸው በመታደግ አምላክነቱን ሊገልጥላቸ
መፈለጉን የሚያመለክት ምሳሌ አድረጎ የፍቅርና የምህረት መልዕክቱን ያስተላለፈ
የጋብቻን ሕይወት ልዩ ልዩ ገጽታዎች ምሳሌ በመጠቀም ነው። *"ፈጣሪሽ ባልሽ ነው፥ ስሙ
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው የእስራኤልም ቅዱስ ታዳጊሽ ነው፥ እርሱም የምድር ሁሉ አም
ይባላል።"* /ኢሳ 54፡ 5፣ ኤር 3፡ 14 እና ሆሴ 2፡ 19-20/

### 2. በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገል ምሳሌነት /ኤፌ.5፡ 23/

ጋብቻ ባል የሚስት ራስ እንደሆነና በክርስቶስ ስልጣን ስር መሆኑን ሲገል
ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደሆነና እርሱም አካሉን የሚያድን መሆኑን የሚያ
ምሳሌነት ያለው ግንኙነት መሆኑን *"ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱ
አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና።"* /ኤፌ 5፡ 23/ የሚለው የእግዚአብሔር ቃ





ያስረዳል። ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ ሚስት ለባሏ በሁሉ ልትገዛ እንደሚገባት የሚያስተምረው *"ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤"* /ቁ 22/ *"ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ።"* /ቁ 24/ የሚለው እውነትም የጋብቻን ምሳሌነት መሰረት ያደረገ ነው::

*"ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ "* /ቁ 25ና 26/ የሚለው የሐዋሪያው ጳውሎስ መልእክትም ባል፡ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ራሱን መሥዋዕት በማድረግ እንደ ወደዳት ሚስቱን ይውደድ በማለት የፍቅርን ልክና የግንኙነት ጥልቀት ይገልጻል። ክርስቶስ አካሉን ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳትና ባል የራሱን አካል እንደሚወድ ሁሉ ሚስቱን ሊወድ እንደሚገባ የሚያሳየው አሳብ ምሳሌነቱ ምን ያክል ጠንካራ እንደሆነ ያስገነዝበናል። *"... እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤"* /ቁ 25፣ 28፣ 30 /:: ባል ከሚስቱ ጋር አንድ ስጋና አካል እንደሆነ ሁሉ እንዲሁ ክርስቶስ ከአካሉ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው አንድነት ምን ያክል ጠንካራ እንደሆነ ከ**ቁ. 30-32** የተገለጠው አሳብ ያሳያል። በጋብቻ ውስጥ ያለው አንድነት በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ግንኙነት በግልጥ በማሳየቱ ምሳሌነቱ የላቀና ከፍተኛ ነው። **ቁ. 32** *"ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ።"* በማለት አጽንኦት የሰጠውም ለዚህ ነው።

### 3. ለጌታ ዳግም መምጣት ያለው ምሳሌነት

የክርስቶስ ኢየሱስን ዳግም መምጣት ድንገትነትና ለመምጣቱ ዝግጁ ሆኖ የመገኘትን አስፈላጊነት ማሳየትን ቀዳሚ ትኩረቱ ያደረገውን የወንጌላት ክፍል መጥቀስ ይህን እውነት ለማሳየት ጠቃሚ ነው:: *"ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አታውቁምና እንግዲህ ንቁ"* /**ማቴ** 25፡ 13/ በማለት ስለጌታ ዳግም መምጣት ለማስረዳት ወንጌላዊው ማቴዎስ ምሳሌያዊ በሆነ መንገድ ጽሑፉን ለመግለጥ ጥረት ያደርጋል። የተጠቀመው ምሳሌ ከአስሩ ቆነጃጅት አምስቱ ዘይታቸውን ሞልተው በማብራት በትጋት ሲጠባበቁ የሚያሳይ የልባም ሴቶች ምሳሌ ነው። ሌሎች ቆነጃጅት ግን በቂ የሆነ ዘይት የሌላቸው፣ እንቅልፍ እንቅልፍ የሚላቸውና እስከ መጨርሻው ሙሽራውን መጠበቅ አቅቷቸው ዘይት ለመግዛት ሲወጡ ድንገት ሲጠብቁት የነበረው ሙሽራ በሌሉበት እንደመጣባቸውና በሩ እንደተዘጋባቸው በምሳሌው ተገልጿል። በእርግጥ ምሳሌው በመጨረሻው ሰዓት ሙሽራው ክርስቶስ ዳግም ሲመለስና ቤተ ክርስቲያን ማለትም አማኞች በትጋትና በጽናት ባለመጠበቃችን ምክንያት ሙሽራው ለእኛ ሊፈርድልን ከመምጣት ይልቅ የሚፈርድብን እንዳይሆን ዝግጁ እንድንሆን ለማሳሰብ የተነገረ ነው/**ማቴ** 25፡ 1-10/:: በዚህ ምሳሌ ውስጥ መምጣቱ የሚጠበቀው ክርስቶስ በወንድ ሙሽራ ምሳሌ መቅረቡንና ወንድ ሙሽራ ካለ ደግሞ ሙሽራውን ጠባቂ ሙሽሪት መኖሯ አይቀሬ መሆኑን እዚህ ላይ ልብ ማለት ያስፈልጋል:: ይህም በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል

ውስጥ የባልና የሚስት ኅብረት የክርስቶስን (የሙሽራውን)ና የቤተ ክርስቲ (የሙሽሪትን) ሕብረት የሚያሳይ ምሳሌ ሆኖ መቅረቡን ያሳየናል:: ስለዚህ ቅ መጽሐፍ *"የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች ደስ ይበለን ሐሤትም እናድርግ ክብ ለእርሱ እናቅርብ።" /ራዕ* 19፡ 7/ እንደሚል ክርስቲያን የሆንን ሁሉ በንቃት፣ በምስ ለእግዚአብሔር ክብርን በመስጠት ራስን በማዘጋጀት ለዳግም ምጻቱ መዘ እንዳለብን በባልና በሚስት ምሳሌነት የተጠቀሰውን ምሳሌያዊ አገላለጽ ልንለማ እንደሚገባን የሚያስታውሰንን የትዳር ኅብረታችን በማየት ሁልጊዜ መን ይኖርብናል።

**በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት ምሳሌነቱ በክርስቶስና በበ ክርስቲያን መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጥ ታላቅ ምሳሌ ነውና የት ግንኙነታችንን በየጊዜው እየጠነከረ እንድሄድ ዕድል እንስጠው!**





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አንድ (1)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የክርስቲያናዊ ጋብቻን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንነት ባካባቢያችሁ ካለው ልማዳዊ አስተሳሰብ ጋር በማነጻጸር በሰፋት ውይይት አድርጉ::
2. በቃል ኪዳንና በኮንትራት ጋብቻ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ከመጽሐፍ ቅዱስና አሁን ካለንበት ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማወዳደር ተወያዩ::
3. እግዚአብሔር ጋብቻን ለሰው ልጆች የሰጠበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዓላማ ምንድን ነው? ከዓላማው ውጭ እየተደረጉ ያሉ ልምምዶችን በማንሳት ተወያዩባቸው::
4. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጋብቻ መርሆች ምንድን ናቸው? መርሆዎችን በመዘርዘርና በማብራራት ተነጋገሩ።
5. የጋብቻ አጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተፈጥሮ/ባሕርይ/ ምንድን ነው ትላላችሁ?
6. የጋብቻን የላቀ ምሳሌነት፣ አስፈላጊነትና በጋብቻ ውስጥ ካለው ግንኙነት ጋር በማያያዝ ግለጡ ውይይትም አድርጉ::